## *ውጭ ጉዳይ ሲገለጥ*

## *የስዩም ነገር*

ውጭ ጉዳይ ሚ/ር ከብሔራዊው ቤተ-መንግሥት ዝቅ ብሎ ከሂልተን ሆቴል ፊት ለፊት ይገኛል። ይህ መስሪያ ቤት ከነ ሙሉ ክብሩና ጥቅሙ ለስዩም መስፍን ከተሸለመ እነሆ 18 ዓመት ሆነው። የዚህ ሰው ቢሮም በህንጻው በሰተሰሜን ጥግ አራተኛው ፎቅ ላይ በቀይ ምንጣፍ ተሸልሞ ይታያል።በሦስተኛዉ ፎቅ ላይ ከስዩም መስፍን ቢሮ በስተ-ደቡብ አንዲት ፐብ (pub) የምትምስል ክፍል በቀይ ምንጣፍ አሽብርቃና በባለ ቀልሞቹ መጠጦች ተሞልታ ሁሌም ዝግጁ ሁና ትገኛለች። በዚህች ክፍል ስዩም መስፍን ከሂለተን ሆቴል ምግብ እያስመጣ ለወዳጆቹ ግብር ያበላበታል ከስራ ሰዓት ውጭም የመስሪያ ቤቱን ታማኝ ሎሌዎች ስብሰባ ይጠራና ብሉ ጠጡ ደስም ይበላችሁ እያለ ሌሎቹን የመስሪያ ቤቱን ሰራተኞች ሁኔታ እየገመገመ ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል።

በዚህች ክፍል ውስጥ በተደረገ ስብሰባ የአንድ ጎበዝ ሰራተኛ ስም ተነሳ።ስዩም መስፍን ከተሽከርካሪ ወንበሩ ላይ ዘና ብሎ ቁጭ እንዳለ የአስተዳደርና ፋይናንስ ሃላፊ ዘርይሁንን ትኩር ብሎ እየተመለከተ“ ለመሆኑ እንዲህ አይነት ሰራተኛ እዚህ መስሪያ ቤት እንዴት ተቀጠረ ?” ብሎ ጠየቀው።ዘርይሁንም “በስህተት” ነው አለ። “በል እንግዲህ ባሰቸኳይ አሰናብተው” ብሎ ቀጭን ትእዛዝ እንደሰጠው በዚያች ቀን በስብሰባው ላይ የተሳተፈ አንድ የትግራይ ወዳጄ ነግሮኛል። ዘርይሁንም ምንም ሳያመነታ ውሳኔውን ለማስፈጸም ተጣደፈ።አንዲት ጥሩ ደብዳቤ ጽፎና ፈርሞ ትግሉ ማናየሁ ማንደፍሮት የተባለ የመ/ቤቱን ሰራተኛ በችሎታ ማነስ ብሎ አባረረ።

ትግሉ ከመቀሌ ዩንቨርስቲ በኢኮኖሚክስ ተመርቆ መ/ቤቱ ባወጣው ማስታወቂያ መሰረት ተወዳድሮ የተሻለ ውጤት በማግኘቱ የተቀጠረ ነበር።ይህ ወጣት ልጅ በእንግሊዘኛ ቋንቋ በሚታተመዉ ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ መንግሥትን የሚተች ጽሁፍ ስለጻፈ ስዩም መስፍን በችሎታ ማነስ ብሎ እንዲባረር ወሰነ።በዚህም የመ/ቤቱ ሰራተኞች ማንኛውንም የመንግስት ድርጊት ከማወደስ በቀር መተቸት እንደማይችሉ አድርጎ የሰራተኛዉን የመናገር ነፃነት ገፈፈዉ።በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል በተነሳው ውዝግብ የድንበር አካላይ ኮሚሽን የሰጠውን ውሳኔ በትክክል አንብቦ መረዳት የማይችል ሚንስቴር ባለበት መ/ቤት አንድ ሰራተኛ በችሎታ ማነስ ተብሎ ሲባረር ታዝበን በጎ ባልሆነ ዝምታ ተዋጥን።ለማንኛውም ያ ጎበዝ ወጣት ልጅ ተባረረ። እነርሱ እየበሉና እየጠጡ ሌላውን በተለይ አማራዉንና ኦሮሞዉን ከስራ ገበታው ላይ አፈናቅለው ጦሙን ያሳድሩታል።እኛ የምናዉቀዉ የወያኔዎች ነፃ ማዉጣት ማለት ይሄዉ ነዉ እንጂ ሌላ የለም።

ይህ መ/ቤት የስዩም መስፍን የሹመት ቦታ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ገንዘብ የሚያጋብስበትም የቢዝነስ ተቋም ነው። በህወሃት ውስጥ የድሃ ገንዘብ መዝረፍ የሚያሳፍርም የሚያስጠይቅም ተግባር ስላልሆነ ስዩም በሚፈጽመው ሙስና የህወሃት አባላት አይገረሙ ይሆናል።።እስከ አሁን እዳየነውና እንደሰማነው በህወሃት ባህል መሰረት ማጭበርበር መስረቅ መዋሸት መግደል ጀግንነት ነዉ እንጂ የሚያሳፍር ብልሹ ተግባር አይደለም።ህወሃትን ሌላ በምን እናዉቀዋለን ከዚህ ከረከሰ መግባሩ ዉጭ ? እንዲህ አይነቱን ዝርፊያ አይተንና ሰምተን ከመገረም አልፈን አገሪቷን እንመራለን ብለው የተሰየሙ ሰዎች እንዲህ በተደራጀ ዝርፊያ ውስጥ በመስማራታቸውና እንዲህ አይነት የሞራል ዝቅጠት ውስጥ በመገኘታቸው ይህም ደግሞ በገዛ አገራችን እየተፈጸመ መሆኑን ስናውቅ አንገታችንን ደፍተን በቁጭት ተቃጠልን።

መቸስ ሰውየው የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ነውና አገሪቷን እየወከለ በየአገራቱ የመመላለስ ልዩ መብት አለው።ከአገር ሲወጣና ሲገባ እርሱ የያዘው ወይም ደግሞ በኮንቴይነር አስጭኖ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባዉ እቃ አይፈተሽም። የፈለገውን ይዞ ይወጣል ያሻውን ደግሞ ይዞ ይገባል።በአንድ ወቅት መርካቶ ውስጥ በአንዲት ሻይ ቤት ውስጥ የሞባይል ስልኮች ከገበያ ዋጋ ባነሰ ይሸጡ ነበር።ለምሳሌ 1000 ብር የሚሸጥ ሞባይል ቀፎ ከዚያ ቦታ ላይ 700 ብር ሲሸጥ እንደነበረ እናዉቃለን።ይህን ንግድ የሚያካሂዱት የውጭ ጉዳይ ሰዎች ሲሆኑ ግብይቱ በሚካሄድበት ወቅት ደግሞ መሳሪያ የታጠቁና የፖሊስ ዩኒፎርም የለበሱ ሰዎች ብርቱ ጥበቃ ያደርጋሉ።ሌላው ነጋዴ የአገሪቷ ህግ በሚፈቅድለት መሰረት ቀረጥ ከፍሎ ግብር አስገብቶ ያዋጣኛል የሚለውን ዋጋ ተምኖ ገዢ ሲጠብቅ ስዩምና ወዳጆቹ ግን አየር ባየር እያጧጧፉ ገንዘባቸውን ያጋብሱታል።ህጋዊ ነጋዴዉን ከገበያ ውጭ እያደረጉ አገሪቷን ወደ መቀመቅ ያወርዷታል።

ስዩም ወደ ውጭ በተጓዘ ቁጥር ከመ/ቤቱ ወጭ እየተደረገና በሶምሶናይት እየተሞላ ይዞ የሚወጣው ገንዘብ አንድም ቀን ተወራርዶ አያውቅም።ይዞ ከሄደው ገንዘብ ምን ያህሉን ተጥቅሞ ምን ያህሉን እንደመለሰ የሚያሳይ የሂሳብ መዝገብ የለም።በአንድ ወቅት ጅቡቲ የደርሶ መለስ ጉዞ ለማድረግ $20000(ሃያ ሽህ) ዶላር ከሂሳብ ክፍል ወጪ ተደርጎ እንደተሰጠው ለሂሳብ ክፍል ቅርበት ስላለኝ አይቻለሁ።ለደርሶ መልስ ጉዞ ይህን ያክል ይዞ ከሄደ ሶስትና አራት ቀን በሚቆይበት ግዜ ምን ያክል ዶላር ይዞ እንደሚወጣ አንባቢ ልብ ይበል።ይህ ሁሉ ብር ጥቃቅን/ልዩ ልዩ ወጭ ተብሎ ይመዘገባል። ከዚህ ብርም ተመልሶ ወደ መ/ቤቱ ካዝና የሚገባ የለም።በዚህ ሁኔታ ስዩም ወደ ውጭ አገር በተጓዘ ቁጥር እየተሸከመ የሚወጣውን ብር አንድም ቀን ኦዲተር አይቶት ስለማያውቅ መጠኑን እንኳን ሌላ ሰው  ራሱ ስዩምም ቢሆን አያውቀውም።ይህ ሰው በስልጣን ዘመኑ በዚህ መልክ የዘረፈው ገንዘብ ከእርሱ ትውልድ መንደር አዲግራት አንስቶ እስከ አዲስ አበባ አስፋልት መንገድ ሊያሰራ ይችላል ብል ማጋነን አይሆንብኝም።

ይህ ሰው ምንም የሞራል ለከት የሌለው መሆኑን አቶ አረጋዊ በረኀ “አጉል ሙገሳ ወይስ እውነተኛ ታሪክ?” በሚለው ጽሁፋቸው ላይ ጽናት(ውዳሴ ስዩም) የተባለውን መጽሃፍ ሲገመግሙ ፀሀፊዉ ስለ ስዩም ታሪክ የተናገረውን ስድስት ትላላቅ ታሪካዊ ውሸቶችን አውጥተው አሳይቶናል።እነዚያን የስዩም ውሸቶች እዚህ ላይ ብንጠቅሳቸው ምን ይለናል ? ***ውሸት ቁጥር አንድ ስዩም በ1965 የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ሊቀመንበር ሆኖ ተመረጠ፤ ውሸት ቁጥር ሁለት ስዩም ሙሴን ለማስፈታት የሸረን አፐሬሽን መራ ፤ውሸት ቁጥር ሶስት ስዩም የዲማ ማርዋ ማስልጠኛ መሪ ነበር፤ ውሸት ቁጥር አራት ሱዩም የሃይል መሪ ሁኖ ሽራሮ ላይ ወደ ውጊያ ገባ ፤ውሸት ቁጥር አምስት ስዩም የድርቅን ችግር በመፍታት መሪ ነበር፤ ውሸት ቁጥር ስድስት ስዩምና በርሁ(አረጋዊ ማለት ነው) በአንድ ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር። ።ይህ*** ሁሉ ውሸት በትግሪኛ ቋንቋ በተጻፈው ጽናት በተባለው መጽሃፍ ውስጥ ይገኛል። ጸሃፊውም ሀይላይ የሚባል ወጣት ነው።ለዚህ ጸሃፊ የመረጃ ምንጩ ደግሞ ስዩም መስፍን ነው ብሎ አቶ አረጋዊ በርህ አረጋግጠው ነግረውናል።ሃይላይ ስዩምን እየጠየቀ ስለ ስዩም ገድል ጽፎ ሲያበቃ ለስዩም አሳየው ስዩምም ደስ ብሎት እንዲታተም መልካም ፈቃዱ ሆነ።ይህ ማፈሪያ የሆነ ከንቱ “ውዳሴ ስዩም” ከነ ውሸቱ በገበያ ላይ ይኖራል።እንግዲህ ስዩምን ድርቅ ባለ ውሸቱ ካልሆነ በቀር ሌላ በምን እናውቀዋለን? ስዩም ምንም ሳያፍር በድፍረትና በኩራት የኛ ያልሆነውን መሬት ከጠበቅነው በላይ ተሰጥቶናል ብሎ በተሌቭዥን መስኮት  ሲናገር አይተነው አንገታችንን ደፍተን አዝነን አላበቃንምን?

## *የድንኳኑ ነገር*

አንድ አንቶኖቭ ከአምስተርዳም ፊሊፐስ ካምፓኒ እቃ ጭኖ ወደ አዲስ አበባ ይገሰግሳል።ዘውትር እንደሚደረገው አንድ አውሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት ከውጭ ጉዳይ የመግቢያ ፈቃድ ማግኘት ይጠበቅበታል።ይህ ፈቃድ የሚሰጠው በፕሮቶኮል ዋና ዳይሬክቶሬት ስር ባለ አንድ ዋና ክፍል አማካኝነት ነው።የሚመጣው አንቶኖቭ ንብረትነቱ የሩሲያ በመሆኑ በኢትዮጵያ የሩሲያ ኢምባሲ ጉዳዩን ይከታተለዋል። በዚሁ መሰረት የመግቢያ ፈቃድ ለማግኘት አንድ የሩሲያ ኤምባሲ ዲፕሎማት አንቶኖቩ የጫነውን የኢቃ ዝርዝር ይዞ ከፈቃድ ሰጪው ሰው ቢሮ ከተፍ ያላል።ይህን እዚህ ጋ እንተወውና ከዚህ በፊት ወደ ሆነው ክስተት እንሂድ።

አንድ ስልክ ከትግራይ ክልል ከወ/ሮ አረጋሽ (የወቅቱ የክልሉ መስተዳድር ዋና ጸሃፊ የነበሩ ናቸው) ቢሮ ወደ ፈቃድ ሰጪው ስው በሮ ይደወላል።ፈቃድ ሰጪው ሰው እንዲህ ካሉ ከፍተኛ ባለስልጣን ስልክ ተደውሎለት ስለማያውቅ ግራ ይገባውና በታላቅ ትህትና “እመቤቴ ተሳስተው እንደሆን እኔ የበታች ሰራተኛ ስለሆኑኩ እርስዎን ሽቅብ ወደ ላይ ለማናገር አልችልም ወደ ሚ/ሩ ቢሮ ላስተላልፎትና እሳቸውን ቢያናግሩ ይሻላል ይላቸዋል” ሴትየዋም “አዎን ልክ ነህ ወደ ላይ እኔን ለማናገር አትችል ይሆናል ግን እኛ ከፈለግን የማናገር ግዴታ አለብህ” ይባላል። አሁንም በትህትና “እሺ እመቤቴ ምን ልታዘዝ ታዲያ?” “አሁን ከአምሰተርዳም ***ለሰደተኞች የሚሆን ድንኳን ተጭኖ እየመጣ ስለሆነ አንቶኖቩ ቀጥታ መቀሌ እንዲያርፍ እንዲደርግ ብለው ቀጭን ትእዛዝ ይሰጡታል”***።ይህ በፈቃድ ሰጪው የስራ ዘመን ሁኖ የማያውቅ እንግዳ ነገር ነበር።ፈቃድ ሰጪውም በትህትና “እመቤቴ ይህ ነገር ከእኔ የስራ ሃላፊነት ውጭ ስለሆነ እንዲህ ማድረግ አልችልም ምናልባት ክቡር ሚ/ሩን ቢያነጋግሩ” ይላቸዋል። “ስዩምን ስላጣሁት ነው” ይሉታል።”እንግዲያውስ ዋና ዳይሬክተሩን ቢያናግሯቸው” ሲል “እሱም ቢሮው የለም ስለተባልኩ ነው”። “እመቤቴ ያሉኝን እኔ ማድረግ አልችልም ልዩ ፈቓድ የሚያስፈልገው ስለሆነ ለአለቆቼ ቢነግሯቸው ይሻላል እኔ መፍቀድ የምችለው አዲስ አበባ እንዲያርፍ ብቻ ነው”። “መልካም

በል ተወው” ይባልና ስልኩ ጆሮው ላይ ይዘጋል።ከዚህ በኋላ አቶ ንዋይ ገ/አብ(የጠቅላይ ሚ/ሩ የኢኮኖሚ ጉዳዮች አማካሪ ናቸው) ወደ ፈቃድ ሰጪው ቢሮ ይደውላሉ።አሁንም ፈቃድ ሰጪው ግራ ይገባዋል ለማንኛውም ብሎ ምን እንደሚፈልጉ ይጠይቃቸዋል።”ከአምስተርዳም የሚመጣው አንቶኖቭ መቀሌ እንዲያርፍ እንፈልጋለንና ፈቃዱን እንድተፈርምና ለሚመለከተው ክፍል እንድታሳውቅ ይሉታል”።ፈቃድ ሰጪውም “ጌታየ እኔ ይህን ማድረግ እልችልም ከሃላፊነቴ ውጭ ስለሆነ ለአለቆቼ ቢነግሯቸው እነሱ ሊፈቅዱ ይችላሉ” ይላቸዋል። “አለቆችህ የሉም ስለተባልን ነው እኮ አንተን የምናናግረው”። “ቢሆንም እኔ ይህን ማድረግ አልቻልም”። በል ተወው ይባልና ስልኩ ጆሮው ላይ ይጠረቀማል።

በዚህ ጊዜ የሩሲያው ዲፕሎማት አንቶኖቩ የጫነውን የእቃ ዝርዝር ይዞ ወደ ፈቃድ ሰጪው ቢሮ መጣ። ዲፕሎማቱ ይዞ በመጣው የእቃ ዝርዝር መሰረት አንቶኖቩ የጫነው ቱባ ቱባ ባለስልጣናቱ እንደሚሉት ***ለሰደተኞች የሚከፋፈል ድንኳን ሳይሆን ከፊሊፐስ ካምፓኒ የተጫኑ ልዩ ልዩ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ነበር***።ፈቃድ ሰጪውም እጅግ ተገረመ ውስጡን አንዳች አይነት ክፉ ስሜት ሲበላው ተሰማው።የሆኖ ሆኖ የመግቢያውን ፈቃድ የሩሲያው ዲፕሎማት ባቀረበለት ሰነድ መሰረት ፈርሞ ወዲያውኑ ለሚመለከተው ክፍል(ለደህንነት፤ለመከላከያ እና ለሲቪል አቪየሽን መ/ቤቶች) አስተላለፈ።በፈቃድ ሰጪው ግምት አዲስ አበባ ካረፈ ነገሩ በሚመለከተው ክፍል እርምጃ ይወሰድባታል ብሎ አስቦ ነበር በፍጥነት ፋክስ ያደረገላቸው።ሆኖም ግን ነገሩ እንዳሰበው አልሆነም።የሩሲያውም ዲፕሎማት አንቶኖቩ ወደ ኢትዮጵያ አየር ክልል መግባት እንደሚችልና አዲስ አበባ እንደሚያርፍ ተነግሮት አመስግኖ ወደ መጣበት ተመለሰ።

ከዚህ በኋላ የሆነው ግን ለፈቃድ ሰጪው ሰውየ አስፈሪ ነበር።በድጋሚ ሁለቱ ትላልቅ ባለስልጣናት ይደውላሉና ይህን መራጃ ከየት እንዳገኘና ለምን አዲስ አበባ እንዲያርፍ ፈቃድ እንደሰጠ ያፋጥጡታል።ፈቃድ ሰጪውም የዋዛ አልነበረምና አንደኛ ይህ ጉዳይ በቀጥታ እኔን የሚመልከት ነው ሁለተኛ እናንተ ያላችሁት ድንኳን ገና አልመጣም ይህኛው አውሮፕላን የጫነው ድንኳን ሳይሆን ኤሌክትሮኒክስ ነው ይላቸዋል። ሁለቱም ባለስልጣናት ከዚህ በኋላ የሚሉት ነገር ስለሌላቸው ስልኩን ጆሮው ላይ እየዘጉ ወደ ሚቀጥለው ተግባራቸው ተሰማሩ።አንቶኖቩን መቀሌ ማሳረፍ።በዚህም በዚያም ተብሎ አንቶኖቩ ከነ ሙሉ እቃው ሌላ ፈቃድ ከውጭ ጉዳይ ሳያስፈልገው መቀሌ እንዲያርፍ ተደረገና እቃውም እዚያው መቀሌ ላሉ ሸሪኮች እንዲከፋፈል ተደረገ። ይህ እንግዴህ የመንግስት ታክስ/ቀረጥ ያልተከፈለበት መሆኑን ልብ በሉልኝ።

ለመሆኑ ያ አንቶኖቭ ሙሉ ኤሌክትሮኒክስ በማን ገንዘብ ይሆን የተገዛው ?የመጓጓዣውንስ ወጭ ማን ከፈለ? እንግዲህ ይህንና ይህን የመሰሉትን የጎደፉ ተግባራት ስናይ ህወሃት ***ማፊያ*** ቡድን ነው መባሉ ትክክል ነው እንላለን።

በመጨረሻም ፈቃድ ሰጭው ከዚህ ክስተትና ከሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ከፈቃድ ሰጭነቱ ተነስቶ ተራ ሰራተኛ ሁኖ እንዲሰራ ከተደረገ በኋላ ከማያውቃቸው ሰዎች ስልክ እየተደወለለት ልዩ ልዩ ማስፈራሪያና የግድያ ዛቻ ይደርሰው ስለነበረ ልጆቹንና ባሌቤቱን ይዞ ተከብሮ የኖረበትን አገር ጥሎ ለመሰደድ ተገደደ።

## *ሰራተኛ ቅጥር*

የመ/ቤቱ ክፍት የስራ ቦታዎች በማስታወቂያ ይወጣሉ አመልካቾች እንዲወዳደሩ ይደረጋል የቅጥርና የደረጃ እድገት ኮሚቴ ፈተና ያወጣል ይፈትናል የተሻለ ውጤት ያላቸው እንዲቀጠሩ ይወስናል።ከዚህ በኋላ በቅጥርና ደረጃ እድገት መመሪያ ውስጥ ያልተካተተ ሌላ ህግ ይመጣል።የኋላ ታሪክ ጥናት የሚባል።ይህን ጥናት  የሚያጠናው አቶ ሃዱሽ ነው። ሃዱሽ የትግራይ ሰው ሲሆን የስራ መደቡ ጥበቃ ሰራተኛ ቢሆንም ዋናው ስራው ግን የአመልካቾችን የኋላ ታሪክ ማጥናት ነው።ሃዱሽ የአመልካቾችን የኋላ ታሪክ በየአድራሻቸው መሰረት በየቀበሌው ወይም በተማሩበት ኮሌጅ እየሄደ እዚያ ባሉት ወኪሎቹ አማካኝነት ልቅም አድርጎ አጥንቶ ሲያበቃ ይቀጠሩ ወይም አይቀጠሩ የሚለውን የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣል።

አንድ ቀን አቶ ሃዱሽ የቢሮየን በር ክፍቶ ገባና ሞባይል ስልኮች ላይ እና ከአዲስ አበባ ውጭ ስልክ መደወል እፈልጋለሁና  ቀጥታ ስልክህን ልጠቀም አለኝ።ፈቀድኩለት።ስልኩን ማይክራፎን ላይ አድርጌ ወደ ፊቱ ቀረብ አደረኩለት። እርሱም የስም ዝርዝር የተጻፈባቸውን ወረቀቶች አውጥቶ ስልኮቹን መደዋወል ጀመረ።የሚያወራው በትግሪኛ ነው።ይህን

የእነርሱን የሚስጥር ቋንቋ ባለመቻሌ ባዝንም ደርግ ኢሰፓ፤አብዮያዊ ዴሞክራሲ አመለካከት፡ህገ-መንግስት፡ፖለቲካ ምና ምን ይል ስለነበረ ምን ለማወቅ እንደሚፈልግ ለመገመት አልቸገረኝም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንዱን በአማርኛ ማውራት ጀመረ።አሁን በንቃት ማዳመጥ ጀመርኩ።ንግግሩን እንዳለ አቀርበዋለሁ፡

“ሃሎ!ማነህ አንተ !? ስሙን የማላስታውሰውን ሰው ስም ጠርቶ እገሌ ነህ ?”

“አይደለሁም”

“እግሌ አለ ?”

“አዎን”

“እስኪ አቅርብልኝ”

“ሃሎ ማን ልበል” አለ አንድ ትህትና ያለው የሚመስል ሰው ከወዲያ ማዶ

“ሃዱሽ ነኝ ያንን ነገር ጨረስክ”

“አዎን አዎን”

“ደህና በል ንገረኝ እስኪ አመለካከቱ እንዴት ነው ?”

“ጥሩ ነው”

“ዋ! ከኦነግ ጋር የሚመሳሰል አቋም አለው ብለውኛል እኮ”

“እኔ እርሱን አላውቅም”

“እንዴት አታውቅም ?”

“እኔ የማውቀው አዲስ አበባ ተውልዶ ማደጉንና 6 ኪሎ ዩኒቨርሲቲ መመረቁን ነው”

“ኦሮሞ አይደልም እንዴ ?”

“ነው”

“ታደያ ከኦነግ ጋር ግኑኝነት የለውም ትላለህ *?”(ይህን ሰሰማ የኦነግን ነገር ማሰላሰል ያዝኩ፤ ምነው ኦነግ ለኦሮሞ ህዝብ ችግር መድረስ አቃታዉ ?በኦነግ ስም በኢትዮጵያዊያኑ ላይ ልዩ ልዩ በደል ሲፈፀም ይህን ግፍ ለማስቆም ምነዉ ለቅም አጣ ?እያልኩ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ፤ኦነግ የኦሮሞን ችግር የማይፈታዉ እኔንና ሌሎች ጭቁን ድሃ ህዝቦችን ሰላገለለ እኛም በፍርሃት ሰለምናየው ነዉ ብየ ለራሴ ነገርኩት።ከዚህ ውጭስ ሌላ ምን ምክንያት ይኖረዉ የሆን ?)* ።ንግግሩ ይቀጥላል፤

“እኔ የማውቀው የአዲስ አበባ ልጅ መሆኑን ነው እንጂ አንተ ሰለምትለው ነገር መረጃ የለኝም”

“እሺ ውጭ አገር ዘመዶች አሉት ?”

“አዎን አሉት አሉ”

“የእነርሱስ አመለካከት”

“ማለት ?”

“እነርሱ ተቃዋሚን ይረዳሉ የሰማሓው ነገር የለም ?”

“የሰማሁት ነገር የለም”

“ኢህአዴግ በሚጠራው ስብሰባ ላይ ይመጣል ?”

“መጥቶ አያውቅም”

“ታዲያ የአመለካከት ችግር አለበት ማለት ነዋ !”

“እኔ እንጃ”

“ምን እኔ እንጃ ትላለህ ይሄን ይሄን ነው እኮ ማጥናት የነበረብህ”

“እኔ የማውቀውን ነግሬሃለሁ”

በል ድህና ሁን ብሎ መልስ ሳይጠብቅ ስልኩን በጆሮዉ ላይ ዘጋው።

ሶስት ሳምንት ፈጅቶ የረባ መረጃ አላመጣም ብሎ ሲናደድ እኔ ተቀብየ ያናገርከው ሰው የአመለካከት ችግር ይኖርበት ይሆን ? ስለዉ ***“ይሄ ቦዜኔ ምን አመለካከት አለው እሱ ደግሞ*** እዚያ ቀበሌ ውስጥ ስራ ቢሰጠውም በአግባቡ መወጣት አልቻለም፥ዝም ብሎ ነው አይረባም” ብሎ ሲያበቃ ሌላ ስልክ መደወል ጀመረ።አሁን የሚያወራው በትግሪኛ ነው እኔ በማልሰማው የእርሱ የሚስጥር ቋንቋ።ከዚህኛው ሰው ጋር ሲያወራ የሚፈልገውን የሚያገኝ ይመስል ነበር።ሁሉንም የአገሪቷን ቁልፍ የስልጣን ቦታዎች ጨካኝ የተወሰኑ ትግሬዎች ይዘዉ የአገሪቷን ስቃይ ማብዛታቸዉ ሳያንስ እንዲህ በየቦታዉ ተሰግስገው የቀሪውን ኢትዮጵያዊ እድል ፈንታ ወሳኝ ሁነው መቀመጣቸው ውስጤን ሲበላው ተሰማኝና ከሃዱሽ በስተረጀባ ያለውን ያን ዘረኛ ስርአት አጥብቄ ጠላሁት።

ሃዱሽ ስልኩን ደውሎ እንደጨረሰ ስም በተጻፈበት ነጭ ወረቀት ላይ አጫጭር ነጥቦችን ጽፎ ሲያበቃ የተወዳዳሪዎቹ ስም በተጻፈበት ስንጠረዥ ላይ ደግሞ በስማቸው ትይዩ የ”ኤክስ” እና “ራይት” ምልክት ያደርግባቸዋል።ይህን የሚያደርገው ፊቴ ቁጭ ብሎ ስለሆነ የ”ኤክስ” ምልክት ሲያደርግ ያየሁትን የአንዱን አመልካች ሁኔታ ጠየኩት፡

እሱ የ”x” ምልክት ያደርክበት አይሆንም ማለት ነው?

“አዎን አይሆንም”

ምነው ?

“ችግር አለበት”

ምንድ ነው ችግሩ ?

“ምን ይሄ ትምክህተኛ ነው።ዩንቨርሰቲ እያለ ደግሞ ይበጥብጥ ነበር። ጸረ ህዝብ ነው።የአመለካከት ችግር አለው። አባቱ ደግሞ ደርግ ኢሰፓ ነበር”

ስለዚህ አይቀጠርም ማለት ነው ?

ምን አንተ ደግሞ የዚህን መ/ቤት ጸባይ እያወክ ትጠይቀኛለህ ? ሲለኝ እርሱ የሚያውቀውን የመ/ቤቱን ጸባይ ባለማወቄ እያዘንኩ ሌላ የ”ራይት” ምልክት ያደረገበትን ጠየኩት፤

እርሱ የ”ራይት” ምልክት ያደርክበት ጥሩ ነው ?

“ይሄ ደህና ነው።የአርሶ አደር ልጅ ነው።ዩኒቨርስቲም እያለ ከት/ቱ በቀር ሌላ ምንም አያውቅም።ዝምተኛ ነው”

ለመሆኑ ህገ መንግስቱን በሙሉ ልቡ ይደግፋል ?ስል ጠየኩት፤

“ወዶ ነው የት አባቱ ይሄዳል ብለህ ነው ?”

አይ እንደው ዝምተኛን ሰው ማመን ይከብዳል ብየ ነው።

“እዚህ ከተቀጠረም በኋላ አመለካከቱን እንከታተላለን ምን ችግር አለ ብለህ ነው ?”

አዎን እንደሱም ይቻላል ለካ።(ከቅጥር በኋላ በሚደረግ ክትትል በርካታ ሰራተኞች እንዲባረሩ ተደርጓል)

የብዙ ብሄሮች አገር በሆነች ኢትዮጵያ ውስጥ ውጭ ጉዳይን በመሰለ መ/ቤት ተመጣጣኝ የብሄር ተዋፅኦ መኖር ሲገባዉ ዋናዉ መ/ቤትና ኢምባሲዎች በትግራይ ብሄር አባላት በብዛት ተይዘዋል።አገሪቷ ባላት ከ35 በላይ በሚሆኑ ኢምባሲዎች ውስጥ ትግሬ የሌለበት ኢምባሲ አይገኝም።በያንዳንዱ ኢምባሲ አንድ ወይም ሁለት ትግሬ ተሹሞ እንደፈለገ ይሆናል።ዘበኛ እንኳ ቢሆን ሌሎች ዲፕሎማቶችን የማዘዝ መብት ያለው ታጋይ ብዙ ነዉ።

በዋናዉ መ/ቤት ደግሞ ሊኖር ከሚገባዉ በላይ የትግራይ ካድሬዎች ተሰግስገዉበታል።አብዛኞቹ በትግል ሜዳ የነበሩና ይህ ነዉ የሚባል ችሎታ የሌላቸዉ ፍፁም ደካማዎች ሲሆኑ ግሩም የሆነ ችሎታ ያላቸዉ ጥቂት የትግራይ ሎጆች እንዳሉም ምስክርኔቴን እሰጣለሁ።

መስሪያ ቤቱ ባሉት የዋና ዳይሬክተር ቦታዎች  ዋና ዋና ቁልፍ የሃላፊነት ቦታዎች በትግራይ ብሄር አባላት ተይዘዋል። ዋና ዋናዎችን ለማሳት ያህል ሙሉጌታ ዘዉዴ የሚንስትሩ ካብኔ ዋና ዳይሬክተር፤ፍስሃ ተስፉ ዋና አማካሪ፤ዋህደ በላይ የመስሪያ ቤቱ የህዝብ ግኑኝነት ዋና ዳይሬክተር፤ መብራት በየነ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጉዳዮች ዋና ዳይሬክተር በመሆን ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል።

የመ/ቤቱ (የመጋቢት 30 1996 ዓ.ም) የሰዉ ሃይል ስርጭት ስታትስቲክስ የሚከተለዉን ይመስል ነበር።

| | |
|---|---|
| ኦሮሞ | 54 |
| አማራ | 169 |
| ትግሬ | 52 |
| ጉራጌ | 42 |
| ሌሎች | 52 |

የህዝብ ቆጠራ መረጃ እንደሚያመለክተዉ የትግራይ ህዝብ ከሲዳማ ከወላያታ ወይም ደግሞ ከጉራጌ ተመጣጣኝ ቢሆንም ከሰንጠረዡ እንደምናየዉ የትግሬዎች ቁጥር ከኦሮሞ በልጦ እናገኛለን። በዚህም በዉጭ ጉዳይ መ/ቤት “proportional ratio” አዉጥተን ስናይ የትግራይ ብሄር አባላት የአንደኝነትን ቦታ ይዘዋል። ይህ የሆነዉ ደግሞ ልዩ ችሎታ ስላላቸዉ ሳይሆን የሌሎች ብሄር አባላት በቅጥርና ደረጃ እድገት ኮሚቴ የሚሰጠዉን ፈተና በከፍተኛ ውጤት ቢያልፉም ልዩ ልዩ ስም እየተለጠፈባቸዉ እንዳይቀጠሩ በመደረጉና የተቀጠሩትም በተለያየ ምክንያት ከመ/ቤቱ ስለሚባረሩ ነው።ይህ መ/ቤት ከመከላከያ ሚ/ር ቀጥሎ የመንግስት ከፍተኛ በጀት የሚመደብለት መ/ቤት ሲሆን የዚህ በጀት ተጠቃሚዎች ደግሞ እነዚሁ ካድሬዎች ናቸዉ ማለት ነዉ።

ከሰራተኛ እድገትና ቅጥር ጋር ተያይዞ መነሳት የሚገባዉ ጉዳይ ደግሞ የትምህርት መረጃ ነዉ።ከውጭ አገር የሚገኝ ማንኛዉም የት/ርት ማስረጃ  በኢትዮጵያ ት/ት ሚኒስቴር የአቻ ግምት ይሰጠዋል።በዚህ መሰረት ከውጭ አገር የተገኘ ማስትሬት ዲግሪ አገር ውስጥ ከሚሰጠዉ ማስትሬት ዲግሪ ጋር አቻ ግምት እንዲሰጠዉ ከመጀመሪያ ዲግሪ በኋላ የተገኘ መሆን ይኖርበታል። ይህ ግን ለታጋዮቹ የሚሰራ ህግ አይደለም።እነዚህ ሰዎች ከአገረ አመስተርዳም በተልእኮ ተማርን እያሉ የህግ ማስትሬት ዲግሪ ይዘዉ ብቅ ይሉና የእደትና የደሞዝ ጭማሪ ይጠይቃሉ።የሰራተኛ አስተዳደር ባለሙያዎችም የት/ርቱን ማስራጃ አቻ ግምት ለማሰጠት ወደ ት/ት ሚኒስቴር ይወስዱና ለሚመለከተዉ ሰራተኛ ያቀርባሉ።ሰራተኛዉም በደንቡ መሰረት አቻ ግመታዉን ሰርቶ ደብዳቤ ይሰጣል በዚያ መሰረት ደሞዝ ጭማሪ ይደረጋል።

አንድ ቀን  የአንድ ታጋይ የማስትሬት ዲግሪ ማስረጃ ለሰራተኛ አስተዳደር ባለሙያ ተላከ።አቻ ግምት ተገምቶ እድገቱ እንዲፈፀም የሚል የተመራበት።የሰራተኛ አስተዳደር ባለሙያም የት/ት ማስረጃዉን ተቀብሎ የአመልካቿን ፋይል ቢያገላብጥ የመጀመሪያ ዲግሪ ማስረጃ ያጣና ወደ ባለ ጉዳይዋ ይደውልና የመጀመሪያ ዲግሪ ማስረጃ ስለሌ አቻ ግምት መስጠት አይቻልም ይላታል።ሴትየዋም ይሄ ከውጭ አገር የተገኘ ት/ት ነዉ ወስደህ ንገራቸዉ ብላ ትእዛዝ ብጤ ታስተላልፋለች።የሰራተኛ አስተዳደር ባለሙያም ከምጨቃጨቅ ብሎ ወደ ት/ት ሚንስቴር ይዞት ቢሄድም እንደማይሆን የሚገልፅ ደብዳቤ ተፅፎ ይሰጠዉና እርሱም አምጥቶ ለባለ ጉዳይዋ ይነግራታል።ሴትየዋም ተቆጥታ ትሄድና ለስዩም ትነግረዋለች ስዩምም የወቅቱ ት/ት ሚኒስቴር ለወ/ሮ ገነት ዘዉዴ ደዉሎ በልዩ ሁኔታ እንዲታይ ቢላት አቻ ግምቱ በገነት ዘዉዴ ፊርማ ታጅቦ ከሰራተኛ አስተዳደር ባለሙያ ቢሮ መጣና ሴትየዋ እድገቱን እንድታገኝ ሆነ።ምንም እንኳ ከመጀመሪያ ዲግሪ በፊት ለተገኘ ማስትሬት ዲግሪ እዉቅና የማይሰጥ ቢሆንም ለታጋዮቹ ግን የሚከለከል አይደለም።ለእነርሱ ሁሉም ነገር በልዩ ሁኔታ ይፈፀማል።በጦር ሜዳ ያሳለፍት ግዜ በሙሉ ቀጥታ አግባብ እንዳለዉ የሥራ ልምድ እየተያዘ ከማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በተለየ ሁኔታ እደገትና ሹመት እየተሰጣቸዉ ይገኛል።

አምስተርዳም ከሚባል አገር የህግ ማስትሬት ዲግሪ ያልተገዛለት የወያኔ ባለስልጣን በቁጥር ሲሆን ለዚህም የሚከፈለዉ ከኢትዮጵያ መንግስት በጀት ወጭ እየተደረገ ነዉ። 12ኛ ክፍል ማጠናቀቃቸዉ በዉል ሳይረጋገጥ በዓለም አቀፍ ህግ ማስትሬት ዲግሪ በተልእኮ ተምሮ ማምጣትና እደገትና ሹመት መጠየቅ የተለመደ ተግባር ነዉ። በእርሻ ሙያ ዲፕሎማ ተመርቀው ካመስተርዳም ባለማቀፍ ህግ ማስትሬት ዲግሪ የጨበጡ ካድሬዎች ብዙ ናቸዉ።

የአንድ መ/ቤት ሠራተኞች  የርስ በርስ ግኑኝነት በመተማመን ላይ የተመሰረተ ቢሆን ለመ/ቤቱ የሥራ ስኬት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። በውጭ ጉዳይ ሰራተኞች መካከል ግን ምንም ዓይነት መተማመንና ግልፅነት የሚባል ነገር የለም።ይህን ነገር በምሳሌ ባሳያችሁ ይቀላል።አንድ ቀን እንዲህ ሆነ ከመ/ቤቱ ክበብ ውስጥ በረፍት ሰዓት ሻይ ቡና እያልን ስለ መሬት መሸጥ አለመሸጥ ሁኔታ እናወራለን በዚያች ሰዓት በዚያች ጠረጴዛ ዙሪያ የነበርን ሁላችንም የመሬት ባለቤቱ ሙብት ያለምንም መሸራረፍ መከበር አለበት የሚል አቋም ነበረን።በዚህ መካከል እኛ ወደነበርንበት አንድ ካድሬ ቢጤ የትግራይ ሰዉ ሲመጣ ያየ አንዱ ድመፁን ከፍ አድርጎና አዲስ መጪዉ እንዲሰማዉ አድርጎ “መሬት ይሸጥ ይለወጥ የሚሉ ጥገኞች ብቻ ሳይሆኑ የቀድሞ ስርዓት ናፋቂዎች ናቸዉ “ ብሎ ሲናገር ሁላችንም ሳቃችንን መቋቋም አቃተን።የመጣዉም ካድሬ ብጤ ‘what is so funny guys “ ቢለን እኛም “Nothing sir” ብለን አደበስብሰን አልፈን ሌላ ወሬ ጀመርን።እንግዲህ የህዉሃት ካድሬዎች/ደጋፊዎች ነን ከሚሉ ሰራተኞች ጋር የነበርን ግኑኝነት ይህን ይመስል ነበር።ማንኛዉንም አገርን የተመለከተ ጉዳይ በነፃነት ቁጭ ብለን ሳንነጋገር እነረሱም እኛን ለማዳመጥና ስሜታችንን ለመረዳት ፍላጎት ሳያሳዩ እንዲሁ ሆድና ጀርባ ሆነን ግዜዉ ያልፍ ነበር።የሆነ ሆኖ ቅንጅት የመጣ ግዜ የተወሰነዉ ሰራተኛ ስሜቱን መደበቅ ባለመቻሉ  በተወሰነ ደረጃ ፍላጎቱን በመግለፅ ለቅንጅት ያለዉንም ድጋፍ በተለያየ መንገድ በማሳየቱ ከመ/ቤቱ የመባረር እጣ ገጠመዉ።

## ቅንጅት ያመጣው  ጣጣ

**ቅን**ጅት መንፈስ ነበር።የነጻነት የእኩልነት የዴሞክራሲ እና የፍትህ መንፈስ።ያ የነጻነት መንፈስ በነፍሰ ገዳዮች ከመዳፈኑ በፊት አብዛኛው የውጭ ጉዳይ ሰራተኛ የቅንጅት ደጋፊ ሁኖ ነበር።ግና ምን ያደርጋል ከውስጥም ከውጭም ጠላቶች ተነሱና ያንን በጎ መንፈስ አዳፈኑት። ነፃነት እፈልጋለሁ ብሎ የተነሳዉን ኢትዮጵያዊም በሞት ቀጡት።ከግድያው በኋላ የውጭ ጉዳይ ሰራተኞች ስብሰባ ተጠሩና መንግስት ሰላም ለማስከበር ሲል በሰልፈኞቹ ላይ የወሰደው እርምጃ ትክክል ነው የሚል አቋም እንዲይዙ ተነገራቸው።ከመ/ቤቱ ሰራተኞች መካከል የህ.ወ.ሃ.ት አባላትና ደጋፊዎቻቸዉ ብቻ ይህን ሃሳብ አድንቀው አሺ ብለው ተቀበሉ።የሌላው ብሄረሰብ አባላት ግማሾቹ አጉረመረሙ ገሚሶቹ ዝምታን መረጡ።

ህጻናት ወንዶች ሴቶች እና አዛውንቶች ደረትና ራሳቸው ላይ በጥይት ተመተው እንዲገደሉ ሲደረግ ምን ብለን ነው ይህን ትክክል ነው ብለን አቋም የምንይዘው ብለው አጉረምርመዋል የተባሉ ከ35 እስከ 40 የሚደርሱ ሰራተኞች እንዲባረሩ ተደረገ።የስራ ልምዳቸውንም የሚገልጽ ማስረጃ እንዳያገኙ ተከለከሉ።በዚህም ላካበቱት ሙያ የሚመጥን ሥራ ማግኘት አቅቷቸዉ ስራ ፈት ሆነዉ ቀሩ። ከእነዚህ መካከልም ሁለቱ ሞቱ።አንዱ መለሰ ተ/ማሪያም(አማራ) የሚባል ሲሆን በብስጭት አሰላ ሂዶ ከናቱ ቤት ውስጥ ራሱን ሰቅሎ ህይወቱን ሲያጠፋ ሌላው አክሎግ እምሩ(አማራና ኦሮሞ) የሚባለው ደግሞ ከስራ ከተባረረ በኋላ እቤቱ ውስጥ ሙቶ ተገኝቷል።በወቅቱ ዝም ያሉት የሌሎች ብሄር አባላትና  ወሬ በማቀበል የተባበሩት የትግራይ ካድሬዎች በየኢምባሲው ሹመት አገኙ።

ዛሬ በየኢምባሲዉ ተኮልኩለዉ የምናያቸዉ ዲፕሎማት ተብየዎች ሁለት ገፅታ ያላቸዉ ናቸዉ። አንደኛዉ የወቅቱን ግድያ አይተዉና አዝነዉ ግን ደግሞ ምንም ማድረግ አንችልም ብለዉ ዝም ያሉ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከላይ የጠቀስናቸዉን የስራ ጓዶቻቸዉን ለማስባረር ወሬ በማቀበል የተባበሩና ወያኔ የፈፀመዉን ግድያ አግባብ ነዉ ብለዉ የሚያምኑ ፍፁም ካድሬዎች ናቸዉ።

## የዲፕሎማቶች ስደትና የስዩም አስተያየት

በዲፕሎማቶች ስደት ኢትዮጵያ ከአገራቱ ሁሉ ቀዳሚውን ስፍራ ትይዛለች።እንደ ስዩም ግንዛቤ ዲፕሎማቶች የሚሰደዱት የኢኮኖሚ ጥቅም ፍለጋ ነው።የውጭ አገር በርገር ስቧቸው።ይህ ሰው ሌሎቹን የሚገመግመው በራሱ ውስጥ እያያቸው ስለሆነ አልፈርድበትም።እነዚህ የህወሃት ታጋዮች ለሚበላና ለሚጠጣ ሙት ነገር ሲሉ ከምድር በታች የማይፈጽሙት ምንም የወንጀል አይነት አይኖርም።ሌላውም ልክ እንደ እነርሱ ይመስላቸዋል።ስለዚህም ዲፕሎማቶቹ ተከብረው የሚኖሩበትን አገር ጥለው የሚሰደዱት የሚበላና የሚጠጣ ነገር ፍለጋ ነው ይለናል ስዩም መስፍን።

እውነቱ ግን ዲፕሎማቶቹ ተከብረው ከሚኖሩበት አገር ይልቅ ስደት መርጠው በሰው አገር እጅግ አስቸጋሪና አስልቺ የሆነ ስራ እየሰሩ ለመኖር የሚመርጡበት ዋናው ምክንያት በገዛ አገራቸው ስደተኛና መጻተኛ ሁነው ከመኖር ይልቅ አንደኛውን የሰው አገር ስደት ይሻላል ብለው ነው እንጂ ስዩም እንደሚለዉ የሜሪካና የአውሮፓ በርገር ስቧቸው አይደለም። በተለያየ ጊዜ የተሰደዱ ዲፕሎማቶች የስደታቸውን ምክንያት አብራርተው ጽፈዋል።

ዲፕሎማቶቹ ብዙ ገንዘብ ወጪ ተደርጎባቸዉ ሳይማር ያስተማራቸዉን  ወገናቸዉን እንዲያገለግሉ ተብለዉ በተለያዩ አገራት ኢትዮጵያን ወክለዉ ይላካሉ።ሁሉም ዲፕሎማት አገሩን የሚወድ ለአገሩም አንዳች በጎ ነገር ለማድረግ የሚመኝና የሚፈልግ ነበር።ሆኖም ግን ይህን በጎ ምኞቱን በተግባር ለማዋል በየኢምባሲዉ የተጎለቱ የህዉሃት ካድሬዎች ከ እነርሱ ፍላጎት ውጭ ምንም ነገር እንዲሰራ ስለማይፈቅዱለት በጎ ምኞቱ ከንቱ ሆኖ ይቀራል።ደፍረዉ የካድሬዎችን ጣልቃ ገብነት የሚቃወሙ ካሉም ዲፕሎማቲክ ፓስፖርታቸዉን እነዲያስረክቡ ይታዘዛሉ እመቢ ካሉም እንዲሰረዝ ላሉበት አገር ባለስልጣናት ያሳዉቁና ዲፕሎማቶቹን ያለ መታወቂያ ባዶአቸዉን ያስቀሩዋቸዋል።ያለ መታወቂያ መገኘት ደግሞ ዲፕሎማቶችን ወንጀለኛ ሰለሚያስብል ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ያን አገር ለቀዉ መሰደድ ወይም ደግሞ የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቅ ግድ  ይሆንባቸዋል።

በዚህ ሁኔታ ተወልደዉ ያደጉበትን አገር ጥለዉና ላለመመለስ ወስነዉ የተሰደዱ ዲፕሎማቶች ቁጥር ብዙ ነዉ።እኔ ባለኝ መረጃ መሠረት የማዉቃቸዉን ሰደተኞች ስም ከዚህ ፅሁፍ በስተመጨረሻ አቀርቤአለሁ።

## *ማዳም ፈለግ*

ማዳም ፈለግ የስዩም ሚስት ነበረች።ኤርትራዊ ነች ብለው የነገሩኝ አሉ እኔ ግን መረጃ የለኝም።ይህች ሴት ኤርትራዊም ትሁን ኢትዮጵያዊ ውጭ ጉዳይ ቢሮ ስትመላለስ ኣይቻታለሁ። ወ/ሮ ፈለግ  ጸጉሯን ፍርዝ አድርጋና ወደ ኋላ ለቃው ካባ ደርባ ፈረሳይኛ ቋንቋ ከምንማርበት ክፍል ስትገባ ሁላችንም ተደምመን አየናት። ይህች ደግሞ ማነች ብለን መጠያየቅ ጀመርን።

አንዱ ድምጹን ዝቅ አድርጎ 'የክቡርነታቸው ጸሃፊ ነች መሰለኝ' አለ።ሌላኛው ተቀብሎ '"ኖ" እኔ ጸሃፊዎቹን አውቃቸዋለሁ ይህችን ግን አይቼያት አላውቅም' አለ። 'ምናልባት ከውጭ ከተመለሱት መካከል አንዷ ትሆናለች አለ" ሌላው ።አንዱ በፍጥነት "እናንተ አግብታ ይሆን እንዴ" ሲል ጠየቀ፤ ይህን ሲሰማ የነበረ ከፊት ለፊታችን የነበረ አንድ ሌላ ተማሪ ትንሽ ወረቀት ጽፎ ላከልን።"ሴትየዋ የክቡርነታቸው ሚሽት ነች" የሚል።የሰው ሚስት በመሆኗ የተናደደው ግለሰብ እንዲህ አለ "ለውጭ ጉዳይ ሰራተኞች በተዘጋጀ ት/ት እርሷ ምን ቤት ነች ታደያ ? እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ሁሉም ሚስቱን አምጥቶ በነጻ ማስተማር አለበት" ሲል አጉረመረመ።ሌላው ደግሞ "አንተ ሚስት የለህ ምን እንዲህ አደረገህ" ሲል አስተማሪው ስም መጣራት ጀመረ።ማዳም ፈለግ! እዚህ ነኝ የሚል ድምጽ ወደተሰማበት ሁላችንም አፈጠጥን።"የክቡርነታቸውን" ሚስት ለማየት።የሚንስትር ሚስት መሆን መልካም ነገር ነው።ይጎው የቤት እመቤቷ ወ/ሮ ፈለግ እቤት ቁጭ ማለት ቢደብራት ልትደበር እዚህ ከእኛ ክፍል ተገኘችና እኛም አወቅናት።

የእቃ ግዢ ሰራተኞች እንደነገሩኝ ከሆነ ማዳም ፈለግ በማስታወቂያ ያየችውንና ቀልቧ የወደደውን ማንኛውንም እቃ ቀጥታ ደውላ ባስቸኳይ እንዲገዛልኝ ብላ ማዘዘ ትችላለች።ሁል ግዜ የእርሷ እቃ ለምን አስቸኳይ እንደሚባል ነው ያማይገባኝ ይላል የእቃ ግገርው ሰራተኛ ወዳጄ።እርሷ ጠይቃ ሳይገዛ የቀረ የእቃ አይነት የለም።የምትኖርበት ቤት የመንግስት ስለሆነ ሁሉም አስፈላጊ ነገር የሚሟላው በመ/ቤቱ ወጭ ነው።ግብር ከፋዩ ቁሞ ይሂድ እንጂ በየ አውደዓመቱ የቤት እቃ ለመቀያየር ማዳም ፈለግ ባለሙያ ነች።

ባለቤቷ አራት አዳዲስ መኪናዎችን በስሙ ይዟል።ሁለቱ የራሱ ሲሆን አንዱ የማዳም ፈለግ አንዱ ደግሞ የልጆች የሽንኩርትና የበርበሬ መግዣ ነው።አራቱም መኪናዎች የየራሳቸው ሾፌሮች አሉዋቸው።እነዚህ መኪኖች ምንም አይነት አስቸኳይ የአገሪቷ ስራ ቢኖርም አይንቀሳቀሱም።ምናልባት እቴ እሜቴ ሽርሽር መውጣት ቢፈልጉና መኪና የለም ቢባሉ የሚመጣውን ጣጣ ማንም ማየት ስለማይፈልግ መኪናዎቹ ሁሌም ዝግጁ ሁነው ነቅተዉ ይጠብቃሉ እንጂ ለመንግስት ስራ አይውሉም።

## የላይብረሪዉ ስብሰባ

በመ/ቤቱ ላይብረሪ ወስጥ ለሰራተኞች ት/ት ይሰጣል።ሰራተኛዉ በሙሉ ሰራ ዘግቶ ሁለት ሳምንት ሙሉ አደንቁዋሪ ት/ት ሲማር ከረመ።ካስተማሪዎቹ መካከል አነዱ ያቅም ግንባታዉ ሚንሰቴር ተፈራ ዋልዋ ነበር።መሬትን በተመለከተ "መሬት አይሸጥም አይለወጥም" "over our dead body" እያለ ማስተማር ሲጀምር አጠገቤ ቀጭ ብሎ የነበረዉ አንድ የከተማ ልጅ ትን ብሎት ሳሉን ማቆም ስላልቻለ ሰበብ ሆነዉና እንደ ወጣ ቀረ።እኔም ትን እንዲለኝ እየተመኘዉ ከዚያ ሙት ክፍል ውስጥ ዉየ በፖለቲካ ዉስጥ "over our dead body" ማለት ካልሞትኩ በቀር ስልጣኔን አለቅም ማለት መሆኑን ተምሬ ዉልቅ አልኩ።ከተፈራ በፊትና በሁዋላ ብዙ ህወሀቶች መጥተዉ ሲያደነቁሩን ሰነበቱ። የማልረሳዉን አንዱን እዚህ ጋ ማንሳት ወደድሁ። ከታወቁት ምሁራን መካከል አንዱ የሆነዉን ዶ/ር ከንፈ አብርሃን።

ዶ/ር ከንፈ አሁንም ሌላዉ ትግሬ ነዉ።እርሱም ይበለፅግበት ዘነድ የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሰላምና የልማት ተቋም ተሰጥቶታል።ከእርሱ ዲስኩር በሁዋላ የተናደዱ የትግራይ ልጆች በድፍረት ተናገሩት።'ተቋሙ የአንድ ሰዉ ብቻ ሆነ ስሙም የዶ/ር ከንፈ ተቋም ነዉ የሚባለዉ የሚሰጠዉም ስልጠና እኛን የሚመጥን አይደለም' ምና ምን እያሉ ዉርጅብኝ አወረዱበት።ዶ/ሩም "እያንዳንድሽ እንዴት እዚህ መ/ቤት እንደተቀጠርሽ እናዉቃለን በችሎታ ቢሆን ኑሮ ቦታሽ እዚህ አልነበረም" ብሎ አምርሮ ተናገር።ከዚህ በሁዋላ ራሱ ስዩም መጥቶ የከስረ ስብሰባ ብሎ አዝኖ ተናገረ።እኛም የስዩምን ሀዘን ሰምተን ዝም አልን።

ዶ/ር ከንፈ ከታወቁት ይሉኝታ ቢስ የህውሃት ሰዎች መካከል አንዱ ነበር።ይህ ሰዉ የኢትዮጵያንና የስዊዲንን ፓስፖርት ይዞ እደ ልቡ የሚኖር ነዉ።አንድ ቀን እንዲህ ሆነ፤ይህ ዶ/ር ከዉጭ አገር ከህግ ውጭ እቃ ያስገባና ቀረጥ መክፈል እምቢ ይላል።ምነዉ ቢባል እኔ የዉጭ አገር ሰዉ ነኝ የምሰራዉም የአማካሪነት ስራ ሰለሆነ የዲፕሎማቲክ መብት አለኝ በመሆኑም እቃዉ ይግባልኝ ብሎ ሙግት ይዛል።እንዲህ ከሆነ ደብዳቤ አምጣ ይባልና ጉዳዩ ወደ ውጭ ጉዳይ ይመጣል።ይህን ጉዳይ የሚከታተል አንድ ሰራተኛ ይህ ሰዉ እንዴት የሁለት አገር ዜጋ ሊሆን ይችላል ብሎ የነገሩን ሕገ ወጥነት ገልፆ ፋየሉን ይመልሳል።ከዚህ በሁዋላ ጉዳዩ ወደ ስዩም መሰፍን ይመራል።ስዩምም የዶ/ር ከንፈ መሆኑን ሲያዉቅ በቀይ ብእር **ይፈቀድላቸዉ** በሎ መርቶ ይመልሰዉና እቃዉ ያለ ምንም ጥያቄ ወደ አገር ወሰጥ እንዲገባ ሆነ።የእቃዉ

ዝርዝር ዲፕሎማቲክ ኢሚዩኒት ስለነበረዉ ምን እንደሆነ ልናዉቀዉ አልቻልንም። እንግዲህ እዩልኝ በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የሁለት አገር ዜጋ መሆን ህገ ወጥ ነዉ።ክንፈ ግን ይችላል።በሌላ ግዜ ደግሞ የኢትዮጵያን ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይዞና ኢትዮጵያን ወክሎ ከሄደበት አገር ሁሉ ለኢትዮጵያዊያን ብቻ በተሰጠ መብት መኪናዎችን እያመጣ ከቀረጥ ነፃ በማስገባት አዲስ አበባ ዉስጥ ይሸጣቸዋል።ከቀረጥ ነፃ ለማሰገባት የራሱ ህግና ደንብ ያለዉ ቢሆንም ያ ህግ ግን ለክንፈና ለመሰል ህወሃቶች አይሰራም ነበር።

ይህ ሰዉ የሚመራዉ ድርጅት ሶስት መልክ  አለዉ።የመጀመሪያዉ ልክ እንደ ወጭ አገር ኢምባሲዎች እቃዎችን ከቀረጥ ነፃ የማስገባት መብት ያለዉ ድርጅት፤ ሁለተኛዉ ምንም እንኳ በዉጭ ጉዳይ ስር የሚተዳደር ቢሆንም እንደ ገለልተኛ የኢትዮጵያ መንግስት አማካሪ በመሆን ሁኔታዎች ሁሉ እየተሟሉለት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች በብዙ ሚልዮን የሚቆጠር ዶላር በእርዳታ መሰብሰብ ፤ሶስተኛዉ የዉጭ ጉዳይ ሰራተኞችን አሰለጥናለሁ በማለት ከፍተኛ በጀት እንዲመደብለት መጠየቅ። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ግሩም የሆነ ሬስቶራንት ከቢሮዉ ስር ያለዉ ሲሆን ከሬስቶራንቱ ጎን ደግሞ አንድ መፅሃፍት መሸጫ መደብር አለ።በዚህ መደብር ውስጥ የክንፈ መፃፎች እየተሸጡ የሚገኘዉ ገቢ ደግሞ ቀጥታ ለክንፈ ነዉ። እንግዲህ በስንት መልኩ የአገሪቷን ገንዘብ እንደሚዘርፉ ልብ በሉልኝ። ለዚህ ነዉ አንዳንድ በስብሰባዉ ላይ የነበሩ የትግራይ ልጆች ተናደዉ ክንፈን በድፍረት ለመናገር የበቁት።የሆነው ሆኖ እኛ ግን ለትግራይ ለጆች የምንመክረዉ ነገር ቢኖር መናደድ ያለባቸሁ ክንፈን በመሰሉ ግለሰቦች ላይ ሳይሆን ለእነዚህ አይነቶቹ ሰግብግብ ባለሰልጣናት ገደብ ባላበጀ በዘረኛዉና በነፍስ ገዳዩ ህ.ወ.ሃ.ት.በዘረጋዉ ደካማ ሰርዐት ላይ ነዉ።ህዉሃትን እየደገፉ ክንፈን መቃወም ቁም ነገር ያለዉ ነገር ሊሆን አይችልም።

በመጨረሻም ያ ከአራት ጫማ በላይ የማይረዝመዉ ዶ/ር ክንፈ አብርሃ ዋናተኞች የሚያደርጉትን ዓይነት ትልቅ መነፅር ከዐይኑ እንደ ሰካ በምድረ ኢትዮጵያ በሰላም ሙቶ ተቀብሯል።የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንም ኢትዮጵያ “ድንቅ ልጇን” አጣች ብሎ እንዳረዳን እርማችንን አዉጥተናል።ክንፈ ቢሞትም ሌላዉ የህ.ዉ.ሃ.ት ከፍተኛ ካድሬዉ ስብሃት ነጋ እየተጎተተ ሂዶ በቦታዉ ተተክቷል።ታዲያ ምን አለበት ከኦሮሞ ከአማራ ከደቡብ ወይም ከሌላ ብሄሮች ዉስጥ ችሎታ ያለዉ ሰዉ ተፈልጎ ሲታጣ  “ሊቁ” ስብሃት ነጋ ቢሾም?!የትግራይ ነፃ አዉጭዎች የታገሉትስ ለዚህ አይደል ? ሊቃነ ዘራፊዎችን ለማዘመን ?!!አይ አገሬ ኢትዮጵያ ለምን ይሆን እንዲህ የቀን ዠቦች የተቀራመቱሽ?

## *ነፃ ተጓዦች*

የወያኔዎችን ብልግናና ይሉኝታ ቢስነት የሚገልፁ እጅግ አፄያፊ ክስተቶችን በአገዛዝ ዘመናቸዉ ተመልክተን አግዚኦ ብለን አብቅተናል። በዉጭ ጉዳይ በኩል የሚፈፅሙትን የስልጣን ብልግና ስናጫዉታችሁ መገረም ወይም ደግሞ ያለመገረም መብታችሁ የተጠበቀ ነዉ።

አንድ ቀን የወያኔዎች ወንድም ወይም ደግሞ የአንዱ ልጅ በሆንኩ ብየ ተመኘሁ።አሁን ቁጭ ብየ ሳስበዉ ግን ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዱ ስላልሆንኩ እግዚአብሄርን አመሰግነዋለሁ።በኩፉዎች መንገድ ያልሄደ እርሱ ምስጉን ነዉ የሚል የመፀሃፉ ቃል ትዝ ስላለኝ።እነሆ የነፃ ተጓዦች ነገር...የእነርሱን ዝምድና ያስመኘኝ አሳፋሪ ነገር፤

የወያኔ ባለስልጣናት ለአንዳች ጉዳይ ወደ ውጭ በተጓዙ ቁጥር ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እየተዘጋጀላቸዉ አጅበዉ የሚጓዙትን ዘመድ አዝማዶች ቁጥር እግዜር ብቻ ነዉ የሚያዉቀዉ።ልጆች ወንድሞች የወንድም ልጆች የሚስቶቻቸዉ ዘመዶች እረ ሰንቱን ቆጥረን እንችለዋለን ዘመዶቼ ?እነሱ ለሸርሽር በሄዱ ቁጥር የዲፕሎማቲክ ቪዛ ሰራተኞች አስቸኳይ እየተባሉ መዋከባቸዉ ግን ያሳዝናል። የግብር ከፋዩ ገንዘብ በእነዝህ ከንቱ ባለስልጣናትና ዘመዶቻቸዉ አማካኝነት እንዲሁ በመባከኑ እጅግ አዝነን ወጥቶልናል።ይህ ሁሉ ወጭ የመ/ቤቱ የሂሳብ አሰራር በሚፈቅደዉ መሰረት የተወሰነ የወጪ ርእስ ስለሌለዉ በሺዎች የሚቆጠር ዶላር ልዩ ልዩ  ወጭ ተብሎ ይመዘገባል።በቃ ማንም አይጠይቀም።

ይህ ሁኔታ የሚፈፀመዉ በዉጭ ጉዳይ ባሉ ባለስልጣናት ብቻ ሳየሆን በራሱ በመለስ ዜናዊ እና በዙሪያዉ በተኮለኮሉ አማካሪ ተብየዎችም ጭምር ነዉ።የአዜብ መስፍን፡የንዋይ ገ/አብ፡የቁጡዉና ትእቢተኛዉ ሙሉጌታ ልጆችና ዘመዶችም ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት እየያዙ በመንግስት ወጭ ሽርሽር እንደሚሄዱ በውጭ ገዳይ በዲፕሎማቲክ ቪዛ ዋና ክፍል ይሰራ የነበረ ወዳጄ አጫዉቶኛል።ኢትዮጵያዊያን በቀን አንድ ዳቦ አግኝተዉ መብላት አቀቷቸዉ በራብ አለጋ

እየተገረፉ ባሉበት ሁኔታ እነዚህ ዋልጌ ባለስልጣናትና ዘመዶቻቸዉ እንዲህ ሲቀማጠሉ ስናይ እረ ለመሆኑ ይህች አገር የማን ነች ብለን እንድንጠይቅ ሆነናል።

## *በመጨረሻም*

በመጨረሻም ይህች አገር የሁላችን እየሆነች አየደለም።በዚህ 18 ዓመት ዉስጥ አገሪቷን የተቆጣጠሯት ጥቂት ማፊያና ዘረኛ ሃይሎች የሰዉ ልጅ ያደርገዋል ተብሎ የማይገመተዉን በደል በኢትዮጵያዊያኑና በኢትዮጵያችን ላይ ፈፅመዋል። ለብዙ ዲፕሎማቶችና ኢትዮጵያዊያን ሞት እንግልትና ስደት ምክንያት ሁነዋል። በእነዚህ ሰውንም እግዚአብሄርን በማይፈሩ ጨካኝ ቡድኖች ዘመን ኢትዮጵያችን በሁሉም መስክ ተዋርዳለች። ዲፕሎማቶቹ በውጭ አገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጋር እየተገናኙ የአገራቸዉን ገፅታ እንዳያድሱ በካድሬዎቹ አጥር ተከልክለዋል። በዚህም ምክንያት ብዙ የውጭ ምንዛሪ ወጥቶባቸዉ የተላኩበትን አገር እየተው መሰደድ ግድ ሁኖባቸዋል።

የዉጭ ጉዳይ መ/ቤት ሰራተኛዉ በካድሬዎች ነፃነቱን ተገፍፎ የሚያምነዉን ሳይሆን የማያምነዉን እየፈፀመ በባርነት ውስጥ የሚኖር ነዉ።ስዩምና አጫፋሪዎቹ ሰራተኛዉ ነፃ ሁኖ ለአገሩ የሚበጅ ነገር እናዳያስብና እንዳያደርግ ወዶና መርጦ ባልሆነዉ ዘሩ እንዲደራጅና በዘሩ ብቻ እንዲተሳሰር በማድረግ እንደ አንድ አገር ዜጋ የጋራ አቋም እንዳይኖረዉ በርትተዉ ይሰራሉ።ለዚያች ድሃ አገር ሊጠቅም የሚችል በጎ ተግባር ከመስራት ይልቅ አንዱ አንዱን ፈርቶና ጠርጥሮ እዉነተኛ ፍላጎቱን ደብቆ በከንቱ ስሜት እንዲባክን ያደርጉታል ።ከዚህ ዓይነቱ ስሜት ወጥቶና ደፍሮ አንድ ሁለት አስተያየት የሰጠ ከተገኘም ያለምንም ቅደመ ሁኔታ እንዲባረር ይደረጋል።

በዚህም ኦሮሞዉ አነግ አማራዉ ነፍጠኛ ሁነዉ እርስ በርሳቸዉ ለአንድ በጎ ዓላማ አንድ ላይ እንዳይቆሙ ለማድረግ የእነዚህን ትላልቅ ብሄር አባላት ልጆች አንድነት ይሸረሽራሉ።አንዱ ለአንዱ ስጋት እንደሆነ አድርገዉ ለማሳየት ይጥራሉ።በተወሰነ ደረጃ የተሳካላቸዉ የሚመስልበት ሁኔታ አለ።አነግ ስልጣን ከሚይዝ ህዉሃት እዚያዉ እየበላኝ ቢቀመጥ ይሻላል ይላል አማራዉ በሌላ በኩል ደግሞ ኦሮሞዉ ነፍጠኛ(አማራዉ) ስልጣን ላይ ከሚወጣ ህዉሃት እዚያዉ ቢቀመጥ እመርጣለሁ ይላል።ህዉሃት የሚመኘዉ የሄንኑ ነዉ፤ በዚህ መካከል ህዉሃት እድሜዉን እያራዘመ የኦሮሞዉንም የ አማራዉንም ስቃይ እያበዛ ያሻዉን እያደረገ ይኖራል።

ባጠቃላይ ባገሪቷ ጥቂቶች ብዙሃኑን ተጭነዉ ብዙሃኖቹ ደግሞ ጥቂቶቹን ተሸክመዉና አሳራቸዉ በዝቶ የሚኖሩባት አገር ነች።ጥቂቶች ታጋዮች ብቻ በልተዉና ጠጥተዉ ሆዳቸዉን ሞልተዉ ደስ በሎአቸዉ የሚኖሩባት ብዙሃኑ ግን የሚራቡባትና የሚሰደዱባት አገር ነች ኢትዮጵያ።እነዚህ ታጋይ ተብየዎች ያ የማይሞላ ከርሳቸዉን ለመሙላት ሲሉ ቢሰርቁ ቢያሳድዱ ቢያስሩ እና ቢገድሉ የሚከለክላቸዉ ምድራዊ ህግ ስለሌለ በአንዲት ጀንበር አሉ የሚባሉ ሃብታሞች ሁነዉ እናያቸዋለን።

በዚህም መሰረት የህወሃት መሪ መለስ ዜናዊ 1.2 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሃብት ባለቤት በመሆን ከዓለም መሪዎች መካከል 11ኛው ሃብታም መሆኑን በተለያዩ ሚዲያዎች ወጥቶ አይተናል።እንደምን ሁኖ እንዲህ ከሃብታሞቹ አገራት በልጦ ሃብታም ሊሆን እንደቻለ መጠየቅ ግድ ይሆንብናል።ወ/ሮ አዜብም የመለስ ዜናዊ ሚስት እናንተ እኮ ድሆች ናችሁ ተብላ ለቀረበላት ጥያቄ መልስ ስተሰጥ በመገረም ማን? እኛ? እረ የማታውቁቱን አታውሩ! እኔ ድሃ አይደለሁም መለስም ድሃ አይደለም ብላ መልስ መስጠቷን አይተን ተደምመናል።

በህዉሃት አገዛዝ ዘመን በዉጭ ጉዳይ መ/ቤት የሚፈፀመዉን በደልና ዝርፊያ በከፊል ለማሳየት ሰሞከር ይህ ነፍሰ ገዳይ ድርጅት(ህዉሃት) ከዚህ የሚማረዉ ነገር ይኖራል የሚል የዋህነት ኑሮኝ አይደለም።ይልቁንም ስለ እኩልነት፤ስለ ፍትህ ፤ሰለ አንድነት፤ስለ ዴሞክራሲ ድምፀቸዉን ከፍ አድርገዉ ሲሚገቱ በነበሩ የአገሪቷ ደግ ለጆች ላይ የሞት ፍርድ በ እነዝህ ነፍሰ ገዳዮች መፈረዱን ከሰማሁ በሁዋላ በራሴዉ አገርና በወንድሞቼ ላይ እንዲህ ዓይነት ፍፁም ኢፍትሃዊ የሆነ ዱርጊት መፈፀሙ ረፍት ሰለነሳኝ እኔም የማዉቀዉን የወያኔዎችን የረከሰ ምግባራቸዉን ልመስክር ብየ እንጂ።እነዚህ ወሮ በላዎች በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ላይ የሞት ፍርድ ለመፍረድ የህግም ሆነ የሞራል መሰረት የላቸዉም።

በገዛ አገራችሁ ላይ ፍትህ ነግሦ ማየት የምትፈልጉ የቀደሞዉ የዉጭ ጉዳይ አባላትና በስደት ላይ የምትገኙ ውድ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ የስደታችሁ ምንጭ ስዩም መስፍን እንደሚለዉ የአዉሮፓና የአሜሪካ በርገር ወይም ደግሞ የሆዳችሁ ነገር ከአገራችሁ በልጦባችሁ አይደለም።ይልቁንም በገዛ አገራችሁ ነፃነታችሁ በጨካኞችና በዘረኞች ስለተገፈፈ እንጂ።ይህ ሰዉ የመሆን ሚስጢራችሁን የገፈፈባችሁ ጨካኝ ቡድን አሁንም የብዙ ኢትዮጵያዊያንን መከራና ስቃይ እያበዛ አገራችንንም እያዋረደ ይገኛል።አሁን በያላችሁበት ሁናችሁ አገራችሁን ነፃ ለማዉጣት በሚደረገዉ ትግል ውስጥ የበኩላችሁን አስተዋፅኦ የምታበረክቱበት ወቅት ነዉ።አገራችሁ ተበታትና በህዝባችሁም ላይ የከፋ ችግር ደርሶ ከማየታችሁ በፊት በየአቅጣጫዉ የሚደረገዉን የነፃነት ትግል በእዉቀታችሁና በገንዘባችሁ እንድታግዙ ጥሪየን አቀርባለሁ።

የመጨረሻዉ መጨረሻ ደግሞ የትግራይ ነፃ አውጭዎች(ሕወሃቶች) ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚጠይቃቸዉ ባህሪያትና ስነ-ምግባራት የሌሉት ከፉ ዘረኛ ድርጅት ነዉ።በዴሞክራሲ እሴቶች ላይ ያላገጠ በነፃነት ስም ሕዝብን ከፋፍሎ ሰብዓዊ መብትን የረገጠ በፍትህ ላይ የተሳለቀና የገዛ አገሩን ክብር ያዋረድ እንደ ህወሃት ያለ እኩይ ድርጅት ታይቶ አይታወቅም።ይህ ከፉ ጨካኝ ድርጅት በምንም መልኩ በሰላማዊ መንገድ በሚደረግ ትግል ስልጣን አይለቅም።ምክንያቱም ወንጀለኛ ድርጅት ነዉ።ይህን ወንጀለኛ ድርጅት ከህዝብ ጫንቃ ላይ ወደዚያ አሽቀንጥሮ ለመጣል ያለዉ መልካሙ መንገድ ለነፃነት ሲባል መተባበርና ጠላትን መፋለም ነዉ።ህወሃት ከውጭ ጠላት ያልተናነሰ በደል ፍፅሞብናል ስለዚህ ጠላት ነው እንጂ ሌላ የፖለቲካ ተፎካካሪ ሊሆነን አይችልም።

በመሆኑም በውጭ ያላችሁና ወያኔን በሚገባዉ ቋንቋ እናነጋግራለን ብላችሁ ትግል የጀመራችሁ ድርጅቶች (ግንቦት 7፤ኦነግ፤አርበኞች ግንባር፡የኦጋዴን ነፃነት ግንባር እና ሌሎችም) ለላቀ ጥቅም ስትሉ ልዩነታችሁን አጥብባችሁ አንዳች አይነት ግንባር መፍጠር ጊዜ የሚሰጠዉ ተግባር አይደለም።ይህን ማድረግ ካልቻላችሁ ግን በግላችሁ ምንም ዓይነት ለውጥ ማምጣት የምትችሉ አይመስለኝም።አንዳች ዓይነት ግንባር ከፈጠራችሁ እኔን ብቻ ሳይሆን ሚሊየን ኢትዮጵያዊያንን ከጎናችሁ በማሰለፍ ይህ ነጻነትን የማያውቅ ነፃ አውጭ ድርጅት ወያኔን እንደ ኢሰፓ ብትንትኑን በማውጣት በፍርስራሹ ላይ ለሁላችንም የምትሆን ነፃ ኢትዮጵያን መፍጠር እንችላልን የሚል እምነት አለኝ።ስለዚህ የኢትዮጵያ የነፃነት፤ የእኩልነት፤ የፍትህ እና የልማት ግንባር አሁኑኑ ይፈጠር ብየ ጥሪ ሳቀርብ በታላቅ ትህትና ነው።

ከሠላምታ ጋር

ዴርቶጋዳ  (የግንቦት ሰባት የመረጃ ምንጭ)

የዉጭ ጉዳይ ሰራተኛ።

ሠላም አንድነት እኩልነት የህግ የበላይነት እና እዉነተኛ ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያችን ይሁን!!!

ታህሳስ 21፤2002

በስደት ላይ ያሉት ዲፕሎማቶችና ሌሎች የውጭ ጉዳይ ሠራተኞች 81 የስም ዝርዝር ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ዮሃንስ ጌንዳ | አምባሳደር | አቡጃ |
| 2 | ፍስሃ አዱኛ | አምባሳደር | ለንደን |
| 3 | ደ/ር ዋቅታሱ ነገሪ | አማካሪ | ሞስኮ |
| 4 | ሰይፈስላሴ ለማ | ሚኒስትር | ንዮርክ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | አልታየ አላሮ | አመካሪ | ቪየና |
| 6 | መስፍን እንዲሪያስ | አማካሪ | ዋሽንግተን ዲሲ |
| 7 | ብርሃኔ ገ/ህይወት | አማካሪ | ብራስልስ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8 | ተሾመ ፍስሃ | አማካሪ | ቶኪዮ |
| 9 | ተስፋየ ደሳለኝ | 1ኛ ፀሃፊ | ዱባይ |
| 10 | እንዳልካቸዉ ሊበን | 1ኛ ፀሃፊ | ቤጂንግ |
| 11 | መስፍን ይማም | 1ኛ ፀሃፊ | ካይሮ |
| 12 | ፀጋየ ደመቀ | 1ኛ ፀሃፊ | ሄግ |
| 13 | ቢኒያም ከድር | 1ኛ ፀሃፊ | ኩዌት |
| 14 | ፀጋየ በቀለ | 1ኛ ፀሃፊ | ለንደን |
| 15 | ብርሃን መስቀል አበበ | 1ኛ ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 16 | ወገኔ አሰፋ | 1ኛ ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 17 | ብርሃኑ በየነ | 1ኛ ፀሃፊ | ሰነዐ |
| 18 | ጥላሁን ወ/ሰሞኦን | 1ኛ ፀሃፊ | ዋሺንግተን ዲሲ |
| 19 | ራሄል ኩመላ | 2ኛ ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 20 | ገነት አበበ | 2ኛ ፀሃፊ | ሄግ |
| 21 | ክንፈ ጌታቸዉ | 2ኛ ፀሃፊ | ቪየና |
| 22 | ጉልቴ ብርሃኑ | 2ኛ ፀሃፊ | ስቶኮልሆም |
| 23 | ጌታቸዉ ሓይሌ | 2ኛ ፀሃፊ | ቶኪዮ |
| 24 | ፀጋየ ኢዳኦ | 3ኛ ፀሃፊ | ዋሸንግተን ዲሲ |
| 25 | አስቴር ሶሎሞን | 3ኛ ፀሃፊ | አቡጃ |
| 26 | ዘላለም ዳዊት | 3ኛ ፀሃፊ | ቤሩት |
| 27 | ፈጠነ ተፈራ | 3ኛ ፀሃፊ | ጂቡቲ |
| 28 | ዋጋየ ብርሃኑ | 3ኛ ፀሃፊ | ለንደን |
| 29 | አፖሎ እጓለ | አታሼ | አቢጃን |
| 30 | ታምራት ዳምጤ | አታሼ | ቤሩት |
| 31 | መጣአለም ስንሻዉ | አታሼ | ዳካር |
| 32 | ጌታቸዉ መኮንን | አታሼ | ጄዳ |
| 33 | ቡሩክ ከተማ | አታሼ | ሃርጌሳ |
| 34 | ፍሬህይወት በላቸዉ | ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 35 | ሄኖክ መንግስቱ | አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 36 | ግርማ በላይነህ | አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 37 | ደጀኔ ጭኮ | አታሼ | ዋሸንግተን ዲሲ |
| 38 | ምንያህል................ | ምሩቅ አታ ሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 39 | ትዝታ ካሳ | አታሼ | ጄዳ |
| 40 | ታምራት አላዊ | አታሼ | ኒዮርክ |
| 41 | ትርስቲ ተካ | አታሼ | ብራስልስ |
| 42 | ሶሎሞን አሰፋ | አታሼ | ፕሪቶሪያ |
| 43 | ብርሃኑ ግዛቸዉ | አታሼ | ናይሮቢ |
| 44 | መሃመድ ሙስጠፋ | ተርጓሚ | ኩዌት |
| 45 | ሃና ካሳ | ፀሃፊ | ዋሸንግተን ዲሲ |
| 46 | መሰረት አክሊሉ | ፀሃፊ | ዋሸንግተን ዲሲ |
| 47 | ሃና ሐይሉ | ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 48 | ትግስት ለሜቻ | ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 49 | ሳባ ሙሉጌታ | ፀሃፊ | ቪየና |
| 50 | አዜብ ስለሺ | ፀሃፊ | ሄግ |
| 51 | ሉቧቧ እንዲሪስ | ፀሃፊ | ሄግ |
| 52 | ልዩወርቅ ደበበ | ፀሃፊ | ኩዌት |
| 53 | ተክለኪሮስ ተፈራ | የአምባሳደር ሾፌር | ኒዮርክ |
| 54 | ወሰን...... | የአምባሳደር ሾፌር | ኒዮርክ |
| 56 | መሃመድ ሴይድ | የአምባሳደር ሾፌር | ሄግ |
| 57 | ወንድወሰን ተ/ማሪያም | የአምባሳደር ምግብ አብሳይ | ኩዌት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 58 | ታሪኳ...... | የፅዳት ሰራተኛ | ኩዌት |
| 59 | ሲሳይ ማሩ | 3ኛ ፀሃፊ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 60 | ታደስ ያዜ | ተ/2ኛ ፀሃፊ | ለንደን |
| 61 | በረከት ሳሙኤል | 3ኛ ፀሃፊ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 62 | ሰላማዊት ዓሊ | 2ኛ ፀሃፊ | ቤጂንግ |
| 63 | ሙሉነህ ዮሃንስ | አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 64 | ኤርሚያስ ኦላና | አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 65 | ዳምጠዉ አሰፋ | 1ኛ ፀሃፊ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 66 | ነብዩ ዳኜ | አማካሪ | ዋሽንግተን ዲሲ |
| 67 | ዳዊት ዘገየ | 2ኛ ፀሃፊ | ዋናዊ መ/ቤት |
| 68 | ታደለ አሰግዶም | 3ኛ ፀሃፊ | ጂቡቲ |
| 69 | እንዳልካቸዉ ታደለ | አታሼ | ደቡብ ኮሪያ |
| 70 | ቢኒያም.... | የ አምባሳደር ሺፌር | ደቡብ አፍሪካ |
| 71 | ዮሃንስ ዳዲ | የ አምባሳደር ሾፌር | ዋሺንግተን ዲሲ |
| 72 | ኤፍሬም ምህረታብ | | ለንደን |
| 73 | የምስራች ..... | 2ኛ ፀሃፊ | ኒዮርክ |
| 74 | እኩሉ ንዳ | አታሼ | ቴላቪብ |
| 75 | ክብሩ ደመቀ | አታሼ | ቤጂንግ |
| 76 | አጥናፍሰገድ ዘለቀ | ተ/2ኛ ፀሃፊ | ቪየና |
| 77 | መላኩ....... | ምሩቅ አታሼ | ዋናዉ መ/ቤት |
| 78 | ዘውዱ ማሩታ | 1ኛ ፀሃፊ | ኦቶዋ |
| *79* | ፈቃዱ በላይነህ | ተ/2ኛ ፀሃፊ | ብራስልስ |
| 80 | ወርቅየ ብርየ | አማካሪ | ብራስልስ |
| 81 | ተስፋየ አባተ | አማካሪ | በርሊን |